᎒

# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ቁጥር 5 ቀን 7/1/67


## ስለሸሹም ዘር ስሉ፣ ትግሉ ይቀጥላል::

ነገሩ ቀደም ብሎ አልቆ ነበር፣ በሰስተኛው ዙር የተቋቋመው ወታደራዊ ደርግ አጤን ወዲያ ብሎ የመንግስትን ስልጣን በእጁ አገብቶ ነበር:: መስከረም 2/67 የመጨረሻው መግለሲት መፉፋት በተግባር ቀደም ብሎ ያለቀውን በህግ ማፅደቅ ነበር:: በጥቂት 'ምርጥ' ወታደሮች የሚመራው ወታደራዊ መንግስት ስልጣኑን ለብቻው መያዙን በይፋ አስታወቀ:: ጨካኙና ወንጀለኛው አጤ ሃይለ ስላሴም 'መለኮታዊ' ስልጣኑን ተገፎ እስር ቤት ገባ::

በ5/1/67 የተሰጠው መግለጫና አዋጅ ቁጥር 2 'በምርጥ' ወታደሮች የሚመራው ደርግ በያዘው ስልጣን እንዴት እንደሚሰራበት የሚያስረዳ ነው:: የትግሉ አንቀሳቃሴ ባለቤትና የመንግስት ስልጣን ምንጭ ለሆነው ሰፊው ሕዝብ ግን የተጣለለት ፍርፋሪ 'ለምርጦቹ' ሃሳብ ማቅረብና ማማከር እንጂ በፍፁም ውሳኔ ውስጥ ሳይገባ፡ራቅ ብሎ አይኑን እንዲያቅለጨልጭ ብቻ ነበር::

ደርጉ ለሰራዊቱ ውስጥ ውስጡን ገለፃ ሲሰጥ የወታደርን አገዛዝ ያወደው ሕዝቡ ያልተደራጀ በመሆኑ ወኪሎቹን መርጦ ለሕዝባዊ መንግስት ሸንጎ ለመላክ ስለማይችል ነው ብሎ መናገር ጀምሮአል:: ይህ መሰረተቢስና ፍፁም የማወናበጃ ሃሳብ ነው:: ጨቋኙና ፈላጭ ቆራጩ የሃይለስላሴ መንግስት መብቱን ገፎት የፖለቲካ ማህበር እንዳያቋቁም ቢደረግም ሰፊው ሕዝብ በእድር፡በሙያና በሌላ ልዩ ልዩ አይነት መንገድ የተደራጀና ብዙ አይነት ማህበራት ያለው መሆኑ ለማንም ግልጽ ስለሆነ፡የተሰጠው ምክንያት 'አያ ጅብ ሳታመካኝ ብላኝ' እንደተባለው ነው::ለመሆኑ ባንድ በኩል ሕዝቡን አትደራጅ እያሉ እያስገደዱ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ አልተደራጀም ብሎ ማማት ትልቅ ቅጥፈት አይሆንም እንዴ?

ሌላው ደግሞ ገና ባላባታዊው አገዛዝ ከስሩ አልተመነገለም:: ወንጀለኞቹም ገና ለፍርድ አልቀረቡም:: በዚህ ሁኔታ ከሰፊው ሕዝብና ከወታደር የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግስት የተቋቋመ እንደሆነ ጠላት ሊያንሰራራና እንደገና ሊመለስ ይችላል የሚል ሰንካላ ምክንያት ነው:: ሕዝቡን በጣም ዝቅ አድርጎ መገመት ነው:: ወዳጅና ጠላቱን ሕዝቡ መለየት አይችልም ተብሎ ይሆን! ይህ መቼም የማወናበጃ ፕሮፓጋንዳ ነው::

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ሕፃን ወይም ደንቆሮ አይደለም:: ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ ያውቃል:: ትናንትና ከሃይለስላሴ ጋር በሕዝቡ ላይ በደል ይሰሩ የነበሩት የጭቆናና የበዝባዥ መሳሪያና ግብረአበሮች ሰፊው ሕዝብ በተለይም ተማሪውና ተራማጆች ከአስር አመታት በላይ የተጋደሉለትን የደም ትግል ፍሬ ለመቀማት ነው ሕዝቡን ከስልጣን ለማራቅ ጥረት የሚያደርጉት፣ ሕዝቡን በስልጣን ውስጥ እንዳይሳተፍ የሚያደርጉት፡ በዚህ በርካሽ እስተባበባቸው ሕዝቡን ሊደልሉት እንደማይችሉ ማን በነገራቸው! ሁሉንም 'ግልጥልጥ አድርገን እንናገረውና' ደርጉን ለጊዜው በቀጥታም ሆነ በስውር መንገድ የሚመሩት 'ምርጥ' መኮንኖች ትናንት መስከረም 6 ቀን ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ቢያደርጉ በሃይለስላሴ ዘመነመንግስት በተለመደው ፋሽስታዊ ዘዴ በመጠቀም ወታደሩ እንዲበታትናቸው አዘዙ፣ ፀረሕዝብና ፀረዲሞክራሲ መልክ አሳዩ:: ወታደራዊው ደርግ የሃይለስላሴን ቦታ በመውሰድ ላይ ነው::

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቆራጥነትና በህብረት በየካቲት ወር ታሪካዊውን የትግል እንቅስቃሴ በይፋ የጀመረው መብቶቹን ለመጎናፀፍና ኑሮውን ለማሻሻል ነው:: ይህንን ሊያደርግ የሚችለው ከራሱ የተውጣጣ የሕዝብ ለሕዝብ በሕዝብ የሆነ ሙሉ ዲሞክራሲያዊ መንግስት በማቋቋም እንጂ ራሳቸውን በሾሙ 'ምርጥ' ወታደሮች በሚመራ የወታደር መንግስት አይደለም:: ይህንን ደህና አድርጎ መገንዘብ ከትልቅ ስህተትና ጉዳት ሊያድነን ይችላል::

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመካከሉና ከጠቅላላው ወታደር በምርጫ የተውጣጡ አባሎች ያሉበት አንድ ጊዜያዊ መንግስት አሁን ራሱን በመሾም ስልጣን የጨበጠውን የወታደር መንግስት እንዲተካው፣ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ/የሕዝብ መንግስት/ አሁኑኑ እንዲታወጅ፣ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በተለይ የንግግር የጋዜጣ የማህበር የመሰብሰብ የሰላማዊ ሰልፍ ወዘተ. ነፃነቶች ካሁኑ ጀምረው ስራ ላይ እንዲውሉ አጥብቆ ሲጠይቅ:በአሁኑ ወታደራዊ መንግስት የሚደረጉትን ፀረዲሞክራሲ ድርጊቶች ይቃወማል::

1. ጊዜያዊ ነው ቢባልም ወታደሩ ለብቻው የመንግስቱን ስልጣን መያዙን
2. የቀድሞውን የሃይለስላሴን አርአያ በመከተል ከፍተኛና ብዙ ስልጣን/ርእሰብሄር: ርእሰመንግስት: የመከላከያ ሚኒስትር ነት:ጠቅላይ ኢታማጆር ነት/ ባንድ ሰው እጅ መከማቸቱን
3. በሕዝብ ደም የተበከሉና ብዙ ግፍ የፈፀሙ:መታሰርና ለፍርድ መቅረብ የሚገባቸው ሹመት በሹመት እየሆኑ ባዲሱ መንግስት ከፍተኛ ስልጣን ላይ መሆናቸውን
4. ለብዙ አመታት ደማቸውን እያፈሰሱ የሃይለስላሴን የግፍ አገዛዝ ሲቃወሙ የነበሩት ተማሪዎች በወታደራዊው መንግስት እንደዋና ጠላት ተወስደው ከመስከረም 2/67 ጀምሮ በስድስትና በአራት ኪሎ አካባቢ መሳሪያ በማስፈርና ወታደር በማሰለፍ ለማስፈራራት መቃጣቱን፣ በመስከረም 6 ቀንም የተማሪዎችን የሰልፍ መብት በመንፈግ ወታደሩ መሳሪያ ይዞ በተማሪ ላይ መዝመቱን
5. በተራማጆችና በሰፊው ሕዝብ ወገኖች ላይ የማሰር: የማስፈራራት: የማሳደድ: የማባረር: ከአዲስአበባ የማስወጣት እርምጃዎች መውሰዳቸውን
6. የሲአይኤ ቡችሎች በደርጉ ውስጥና አካባቢ መኖራቸው እየታወቀ ምንም አይነት እርምጃ ካለመወሰዱም በላይ ከፍተኛ ቦታ እንዲሰጣቸው መደረጉን
7. የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከሃይለስላሴ ባላባታዊ አገዛዝ ጋር በመሻረክ የእጅአዙር ቅኝ ግዛት አድርጉአት እንደነበረ ሲታወቅ ስለዚህ ዋና ጉዳይ ምንም እርምጃ አለመወሰዱን
8. ሰፊው ሕዝብ የንግግር የጋዜጣ የማህበር የመሰብሰብ ወዘተ. መብቱንና ነፃነቱን መገፈፉን
9. ደንበኛና ትክክለኛ አቋምና ፕሮግራም እስካሁን ድረስ ሳይቀየስ:ጭሰኛውና ደሃው ገበሬ በባለመሬቶች ያለርህራሄ ሲጨቆንና ሲበዘበዝ:ሰራተኛው ከስራ ሲባረር:በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠር ሕዝብ ያለምንም ስራ በረሃብና በችግር ሲኦል ውስጥ እየሰመጠ ሲሄድና የአገሪቱም ኢኮኖሚ እየተንኮታኮተ ውልቅልቁ ሲወጣ:ምንም አይነት እርምጃ አለመወሰዱን አጥብቀን እንቃወማለን::

ዲሞክራሲ ያሸንፋል
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::

## ጠንካራ መንግስት ምንድነው?

ባለፈው ሳምንት በዚሁ ጋዜጣ ቁጥር 4 ያገራችን ጊዜያዊ የትግል እንቅስቃሴ ሊወስዳቸው የሚችል ሁለት አቅጣጫዎችን አመልክተን ነበር:: የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል እንደሚባለው ከነዚህ አቅጣጫዎች የሰፊውን ሕዝብ ጥቅምና ፍላጐት የሚፃረረው አስጊ አቅጣጫ ተወስዷል:: እንደተነገር ነው 'ጊዜያዊ' መሆኑን በናምንም ባናምንም የወታደር መንግስት ታውጆ የመንግስት ስልጣን በጥቂት ሰዎች እጅ ተከማችቶአል::

የትልቁ ዘንደ የቀዳማዊ ሃይለስላሴ ከስልጣን መውረድ ቀደም ሲል በሕዝቡ የተጠየቀና የሚደገፍ ሲሆን፣ ደርጉ ባገሪቱ ላይ ወታደራዊ አስተዳደርን ማወጁ ለሰፊው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን: በዲሞክራሲያዊ መንገድ ደርጉ እንዲወክለው ለመረጠው ለመላ ሰራዊቱና ሕዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም ለሚከራከሩት ለሰራዊቱ ንኡስ ደርጎች /ለምሳሌ ለአየር ሃይል:ለመሃንዲስ መምሪያ:ለአርሚ አቪሽን ወዘተ. ንኡስ ደርጎች/ እንደዱብ እዳ የተጣለባቸው:ሰፊ ምክር ያልተደረገበት:ፀረ ዲሞክራሲያዊ ድርጊት ነበር:: ውሳኔው በደርጉም ውስጥ ቢሆን ጊዜ ተወስዶ ታስቦበት የተደረገ ሳይሆን፣ ጥቂቶች ሰዎች ውጭ ያዘጋጁትና በደርጉ ጠቅላላ ጉባኤ ውስጥ በሽንገላ እንዲያልፍ ያደረጉት ውሳኔ መሆኑን ብዙ ምልክቶች ያሳያሉ::

ስልጣን አልፈልግም፣ ባፍንጫዬ ይውጣ በማለት ሲምል ሲገዘት:ዳርዳሩን ሲሽከረመም ሰንብቶ አሁን እስልጣኑ ኮርቻ ላይ ጉብ ያለው ደርግ ወታደራዊ አስተዳደርን ሲያውጅ የሰጠው ምክንያት 'ጠንካራ መንግስት ያስፈልጋል' የሚል ነው:: ጠንካራ መንግስት ምንጊዜም ያስፈልጋል:: እንዲያውም መንግስት ሁልጊዜም ጠንካራ መሆን ይገባዋል:: ግን ወታደራዊው ያስተዳደር ደርግ የመንግስት ጥንካሬ ምንጩ ምን እንደሆነ ያውቅ ይሆን? ስለጠንካራ መንግስት ሲናገር በሳንጃና በጠመንጃ ላይ የተመሰረተ ጥንካሬ ማለቱ ይሆን? ለዚያ ለዚያማ የሃይለስላሴስ መንግስት ጠንካራ ነኝ ይል አልነበረም? ሕዝቡን በመከፋፈልና የተቃውሞ ሃይሉን መበታተን፣ የዋሁን በስብከት በማታለል፣ አድርባዩን በጥቅም በመግዛት፣ ለመብት ታጋዩን በሳንጃና በጠመንጃ ፀጥ በማሰኘት ለጊዜው እውነትም ጠንካራ ይመስል ነበር፣ በነበር ቀረ እንጂ:: ታዲያ የሃይለስላሴ መንግስት ውሎአድሮ የብዙሃኑ ሕዝብ ጠላት መሆኑና እውነተኛ የሕዝብ ድጋፍ እንደተነፈገው በግልጽ ተረጋገጠ:: ጥንካሬውም በአሸዋ ላይ እንደተገነባ ቤት እንደነበር በማያጠራጥር አኳኋን ተገለጠ:: እርግጥ ነው፣ ሃይለስላሴን ከስልጣን ለማውረድ ከሃምሳ አመት በላይ ፈጅቶአል:: አሁን ግን ሕዝቡ መብቱን ስላወቀ መብቱን ተገፍፎ በቀላሉ ሊገዛ እንደማይችል ደርጉ ሊያውቀው ይገባዋል::

በሳንጃ በጠመንጃና በማጭበርበር ላይ የተመሰረተ የመንግስት ጥንካሬ የአገዳ ምርኩዝ: ፀረሕዝብ ጥንካሬ ነው፣ ውሎአድሮ መሰበሩ አይቀርም:: እውነተኛ አስተማማኝና ዘለቄታ ያለው የመንግስት ጥንካሬ በሰፊው ሕዝብ ፈቃደኝነት:ስምምነትና ተባባሪነት ላይ የተመሰረተ ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ ጠንካራና ዘላቂ መንግስት ሊቋቋም ይችላል ብሎ ማመን ራስን ማታለል መሆኑን ታሪክ ደጋግሞ አሳይቶአል:: አድሃሪያኖች ታሪክን አያምኑም እንጂ::

እርግጥ ጥይት ሲተኮስ:ሳንጃ ሲመዘዝ ለጊዜው ለማስፈራራት ያገለግል ይሆናል:: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የጥይት ምጽዋትም ለማስደንገጥና ለማስፈራራት ይበቃ ይሆናል:: ነገር ግን የእውነተኛ ጥንካሬ መሰረት ሊሆን አይችልም:: ሰፊው ሕዝብ ለመብቱ ለመዋጋት ክንዱ ለክንዱ: ትከሻ ለትከሻ ገጥሞ ከዘመተ ጠላቱን በገዛ መሳሪያው ሊደመስስ ስለሚችል ምንም አይነት መሳሪያ አይበግረውም:: መትረየስ ቢተኮስ:ታንክ ከፊቱ ቢደገን መፍራት የለበትም::

ስለዚህ ደርጉ የመንግስትን ጥንካሬ የሚለካው በመሳሪያ ብቻ ከሆነ በህልም አለም ውስጥ እንደሚገኝ መረዳት አለበት:: ጠንካራ መንግስት የሚገኘው ሕዝቡ ራሱ ወኪሎቹን በመምረጥ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ሲመሰርት ነው::

እስካሁን በደርጉ ላይ የሚቀርበው ትችት በሙሉ በሶስት ዋና አሳቦች አካባቢ ነው:: በትግሉ እንቅስቃሴ ውስጥ የሰፊው ሕዝብ በተለይ የከተሜው ሱታፌ ጉልቱ እንዳይታይ ተጽእኖ ማድረጉ:ባላባታዊ አገዛዝ ከስሩ እንዳይነቀል ሲያሽሞነሙን በመከረሙና ኢምፔሪያሊዝምን ጨርሶ ባለመንካቱ ነው:: እርግጥ ወታደሩ ብቻውን በተለይም ደርጉ ብቻውን ባላባታዊ ስርአትን ያጠፋል ብለን አንገምትም:: ከአቅሙ በላይ ይሆንበታል:: እዚህ ላይ ዋናው ቅሬታ ሰፊው ሕዝብ በተለይ ሰራተ

ኛውና ገበሬው ለዚሁ ተግባር እንዲዘጋጅ ባለመበረታታቱና እንዲያውም በመከልከሉ ነው፣ ሕዝቡ እየተደራጀ በትግሉ ለመሳተፍና ትግሉን ለማፋፋም በሚጥርበት ጊዜ አትሰብሰቡ፡አትሰለፉ፡እኛው እንሰራ ቁጭ ብላችሁ ተመልከቱን በማለቱ ነው። ታዲያ ምን ሆነ? እነሃይለሰላሴ ተያዙ፣ አንዳንድ ነገሮች ተወረሱ፣ ስርአቱ እንዳለ ነው፣አልተነካም፣ የብዙ ሕዝብ መብት የገፈፉ፡የንፁህ አገርወዳድ ደም ያፈሰሱ ባለስልጣኖች አሁንም በስልጣን ላይ አሉ። ታዲያ ይህንን ነው መሰረታዊ ለውጥ ተደረገ ብላችሁ የምትናገሩት?

በኢምፔሪያሊዝም በኩል የደርጉ አቋም ከጥርጣሬ አልፎ እየተረጋገጠ በመሄድ ላይ ነው። በኢምፔሪያሊስት ገፈፋና ተጽእኖ በቀረቀዘች አገር ለጥቂት ቀናት ሳይሆን ለሶስት ወራት ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የቆየው ደርግ አንዳችም ፀረኢምፔሪያሊስት መግለጫ አለመስጠቱ ጥገኝነቱን ለመሸፈን እንዳይሆን ያስጋል።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን እንዳያስቆጣ የሚፈራና የሚሸቆጠቆጥ መንግስት ከርሱ ተጽእኖ ያልተላቀቀ፡የጥገኝነትን ጉዳትና ውርደት ገና ያልተገነዘበ መንግስት አለበለዚያም እንደነሃይለሰላሴ የሌባና የአጭበርባሪ መንግስት ብቻ ነው። እንደዚህ አይነቱ መንግስት አገሪቱን ወደመቀመቅ ይሰዳታል እንጂ አያሻሽላትም፣ አያራምዳትም። ይህ ደህና ተደርጎ መታወቅ አለበት። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን የጥገኝነትና የብዝበዛ ዣንጥላ አሸቀንጥሮ መጣል በተለይ ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ በጣም አስፈላጊ ነው።በዚህ አቅጣጫ ባለው ትግል ላይ ብርቱ ጥረት ማድረግ የሚያስፈልገውም ለዚህ ነው። ነገሩ ፊት ወደፊት ነው አቅጣጫ በመሄድ ላይ ነው። (የሲአይኤ ቡችሎች በአስተዳደሩ ደርግና እርሱ በመሰረተው መንግስት ውስጥ ጉላ ብለው መታየት ጀምረዋል። ይህ እንዳይሆን ጠንካራው መንግስት። በኢምፔሪያሊዝም የሚደገፍ ጠንካራ መንግስት አናውቅም፣ ታሪክ አያስተባብለንም።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በገንዘብም ሆነ በመሳሪያ መልክ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል። የሚሰጠው ግን እርግጠኛ ሲሆን ነው፣ አስር ነው። ለመበዝበዝ እንዲመቸው ሲሆንለት፡መንግስቱ አሜን ብሎ ሲሰግድለትና የፈለገውን ያህል ሕዝቡን እንዲዘርፍ በር ሲከፍትለት ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብስ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ከሃያ አመት በላይ ያውቀው የለም እንዴ? ሕዝቡ ይህን አልደገፈም። የኢምፔሪያሊዝም ጥገኝነትን ምንጊዜም ቢሆን አይደግፍም። ዋና ጠላት ነውና።

በሌላ በኩል ደግሞ ለደርጉ ከየቦታው የተሰጠው ድጋፍ መልክ የያዘና ወሰን ያለው እንጂ ሙሉ በሙሉ በጭፍኑ አይደለም። በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የአስተዳደሩ ደርግ የተደገፈው የሃይለሰላሴንና ያንዳንድ ግብረአበሮቹን ጉድና ወንጀል ዘርዝሮ ከስልጣን በማውረዱ ብቻ ነው። መንግስታዊ ስልጣንን ደርጉ መውሰዱን፣ ባንዳንድ ሰዎች እጅ ስልጣን አለቅጥ ማከማቸቱን፣ የሃይለሰላሴ መንግስት የስለላ ድርጅት/የፀጥታ መስሪያ ቤት/ መሪ ሆኖ የሕዝብን አፍ በማሰር፡መብት በመገፈፍና የብዙ ንፁሃን የአገር ተቆርቋሪዎችን ደም በከንቱ ያፈሰሰውን ነፍሰገዳይ የኮሎኔል በላቸው ጀማነህን በአገር ግዛት ሚኒስትርነትና እንደሚወራውም የደርጉ ምክትል ሊቀመንበር ሆኖ መሾሙን አይደለም። እነዚህን ሕዝቡ አይደግፍም። በራሱ ላይ መፍረድ ይሆናልና። ራሱ በጊዜው ፖለቲካ ትግል እንዳይሳተፍ ተከልክሎ በአጨብጫቢነት ደረጃ ብቻ ተቀምጦ እንዲመለከት መገደዱንስ ሕዝቡ እንዴት ይደግፋል?

ወታደራዊው 'ጠንካራ መንግስት' ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመለከት፡የሚያወራውንና የሚሰራውን ስናገናዝብ፡የደርጉ እርምጃ ከጠቅላላው ወታደር ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚስማማና ምን ያህል እንደሚለያይ ስናመዛዝን የዚህ አይነቱ መንግስት ምን ያህል ዘላቂነት አለው ብለን እንጠይቃለን። መልሱ ከባድ አይሆንም። ዞሮ ዞሮ የአንድ መንግስት እውነተኛ ጥንካሬ የሚመነጨው ሕዝቡ ከሚሰጠው ድጋፍ ነው። ሕዝቡን የማይወክል፡ሕዝቡ የማይሳተፍበት፡የሕዝቡን ፍላጎት የማያሟላ መንግስት ለጊዜው ቢደነፋና ቢያስፈራራም እውነተኛ ጥንካሬ የለውም፣ ደካማ ነው። መንግስት የሚጠነክረው የሕዝቡ መንግስት ሲሆን ነው፣ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሲመረጥ ነው፣ የሕዝቡን፡በተለይም የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም ሲጠብቅ ነው፣ የሕዝቡን መሰረታዊ መብቶች ሲያምንባቸውና በስራ ላይ እንዲውሉ ሲያደርግ ነው። ይህን የማያደርግ ሁሉ ጥንካሬው እጅግ በጣም የተወሰነ ነው። ያለሰፊው ሕዝብ ጥንካሬ የለም።

## ያልተብራሩ አላማዎች

ሶስተኛው ዙር የጦር ሃይሎች እንቅስቃሴ ከተጀመረ እነሆ ከሶስት ወር በላይ ሆነው:: በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ደርጉ አንዳንድ ነጠላ ድርጊቶችን /ባለስልጣኖችን ማሰር: የሃይለስላሴን ሃብት መውረስ: ሃይለስላሴን ከስልጣን ማስነሳት: ወዘተ./ ከመፈፀም በስተቀር ጠለቅ ብሎ ሰፊው ሕዝብ ከየካቲት ጀምሮ ያነሳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ሊያሟላ የሚችል ፕሮግራም እስካሁን አላወጣም:: የሕዝብ ወገን የሆኑ ተራማጆች እንደዚህ አይነቱ የተሟላ ፕሮግራም አስፈላጊ መሆኑን ደጋግመው ከመግለጽ ካለመቆጠባቸውም ሌላ ጠቃሚነት ያላቸው በርከት ያሉ ንድፎች መቅረባቸው የታወቀ ነው:: ታዲያ ደርጉ ደንበኛ ፕሮግራም ለማውጣት ምን ይሆን ችግሩ? እንዲሁም 'ኢትዮጵያ ትቅደም' ሲባል የርእዮተአለም ይዘቱ ምን ይሆን? ምን ይዘን ነው የምንጓዘው? ሰፊው ሕዝብስ ምን አይቶ ለወታደራዊው አስተዳደር ድጋፍ ይሰጥ! ሃይለስላሴ ተነስቶ ሌላ ሃይለስላሴ ላለመተካቱ ዋስትናችን ምን ይሆን! የሰፊውን ሕዝብ የእለት ኑሮ በሚመለከተው በኩል 'አንድም ታለበ ሺ ያው በገሌ' ከተባለው አልፍ የባሰ አታምጣ ከማለት እንዳያደርስ ያሰጋል::

ደርጉ እስካሁን በከባድ ቃላት የተካቡ መግለጫዎች ከመስጠት በስተቀር ወደውስጥ ሰቅስቆ ገብቶ ችግራችንን ሊፈታ ያሰበ አይመስልም:: ለምሳሌ ደርጉ እንደተቋቋመ ያወጣው ባለ13 ነጥብ 'አላማ' ፍፁም የተወናበደና ያልተብላላ ከመሆኑም ሌላ ወደስራ ለመተርጎም የሚያስቸግር:በፊት ሃይለስላሴና እንዳልካቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰጡት ድፍን ተስፋ የማይሻል ነው:: ይህ ሲገርመን መስከረም 2/66 ሃይለስላሴን በማስወገድ ስልጣን ሲጨብጥ ደርጉ ያወጣቸው ባለ15 ነጥብ 'አላማዎች' አፍ ጭራቸው የማይያዝ፣ በተቻለ መጠን ከመሰረታዊያኑ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ለመሸሽ ትልቅ ትግል የተደረገባቸው፣ ደርጉ እራሱ መሰረታዊ ለውጥ ለማድረግ ያልፈለገ መሆኑን ይከስትበታል:: ዋና ዋና ጥያቄዎችን በተወናበዱ ቃላት ሸፍኖ ፍፁም አግባብ የሌላቸውን ጉዳዮች በዝርዝር ያቀርባል::

የመጀመሪያው አላማ ደርጉ 'የማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኩልነት:ይኸውም የገበሬው:የወዛደሩና የሌላውም ጠቅላላ ሕዝብ መብትና እድገት በሚገባ እንዲጠበቅለት ያደርጋል'ይላል:: እዚህ ላይ ጠቅላላ ሕዝብ ሲል ምን ማለቱ ነው? በዝባዡም እንዲበዘብዝ:ተበዝባዡም እንዲበዘበዝ 'መብትና እድገት'ይጠበቅለታል ማለት ይሆን? መብትስ ሲባል የምን መብት ነው! እድገትስ የምን አይነት እድገት! እነዚህ ማብራሪያ የሌላቸው ተጨባጭ ያልሆኑ ቃላት በትናንቱ ጨቋኞችስ በየጊዜው ይወሩ አልነበር? ደግሞም የሕዝቡ መብት የሚጠበቅ ከሆነ ሕዝቡ የመሰብሰብ:ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመደራጀት መብቱን ለምን ተገፈፈ! ደርጉ ለምን ድፍረት ገዝቶ ሃሳቡን ግልጥ በሆነ መንገድ አያቀርብም?

ሁለተኛው አላማ 'በጎሳና በሃይማኖት የተመሰረተውን መለያየትና የኑሮ መራራቅ 'ኢትዮጵያ ትቅደም'በሚለው አላማ መሰረት ያስወግዳል'ይላል:: ኢትዮጵያ ትቅደም የሚለው አላማ ራሱ በብዙ በተለያዩ መንገዶች ሊተረጎም የሚችል ሲሆን እንዴት ችግርን ያስወግዳል ተብሎ ተስፋ ሊጣልበት ይቻላል! በመሰረቱ 'ኢትዮጵያ ትቅደም'ሲባል የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ጥቅም ይቅደም:ኑሮው ይሻሻል ወዘተ. መሆን ሲገባው፣ ደርጉ ግን እርስበርሳቸው ተፃራሪ በሆኑ አግጣጫዎች ይተረጉመዋል:: አንዳንዴ ምድሪቱን:አንዳንዴ ሕዝቡን በጠቅላላ:አንዳንዴም ሰፊውን ሕዝብ ብቻ በሚጠቅስ መንገድ ይተረጉመዋል:: እስካሁን ጥርት ያለ ትርጉም አልሰጠውም::

በ3ኛው:5ኛው:8ኛው:9ኛውና 10ኛው አላማዎች ስለመጥፎ ባህሎችና ሞራል መጥፋት:ስለ ፍርድ መስተካከል:ስለመላው ህብረተሰብ እኩልነት:ስለመብትና ስለብሄራዊ ስሜት ያወራሉ::እነዚህ ሁሉ ያው በደነዘ ቃላት የተፃፉ ከመሆናቸውም ሌላ የነዚህ መሰረት የሆነው የኢኮኖሚ እኩልነት ተድበስብሶ ቀርቶአል:: እንደሚታወቀው በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የኑሮ መለያየት:የፍትህ መጓደል: 'ከራስ በላይ ነፋስ' የሚለው ዘይቤ የሚያይለው የህብረተሰቡ አባሎች በመደብ ተከፋፍለው አንደኛው ሌላውን ሲበዘብዝና ሲጨቁን ነው:: የሃብት መለያየት ካለ በዝባዥና ተበዝባዥ:ጨቋኝና ተጨቋኝ: የፍትህ መጓደልና መንዛዛት: የሚያደናቅፉ 'ባህላዊ እምነቶችና ዘይቤዎች'ይኖራሉ:: የኢኮኖሚ መደላደል ሳይኖር ሌሎቹን ችግሮች ለወጣ ቢሉ በጭ የማይል ጉዳይ ነው:: ባጭሩ 'የኢኮኖሚ ደረጃን ማስተካከል እሹ፣ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል'ብንል ከእውነት አንርቅም::አላማዎቹ ከባህልና ከሞራል ይልቅ ወደነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ማተኮር አለባቸው::

4ኛው አሳብ ስለመሬት መሻሻል ያወራል፡፡ ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ አርሶአደርና ወዝአደር መሰረታዊ ጥያቄ፡የአገሪቱም ቀት ሸረት የሚለይበት ሲሆን ደርጉ በዚያው በተምታታ ዘዴ አልፎታል፡፡ '...ይህ እስከሆነ ድረስ ጭሰኛ የሆነ ሁሉ በሰፈረበትና በሚያርሰው መሬት ላይ የመኖርና የመጠቀም መብትና ይኖረዋል...' የሚለው በትክክል ምን ማለቱ ነው? ጭሰኛው ለባለመሬቱ ሲሶ አኩል ወዘተ. ያፈስባል ወይስ የመንግስት ገበር ብቻ እየከፈለ የድካሙን ዋጋ በሙሉ ይጠቀምበታል ማለት ነው? ይህ አፍፋፍ ሁኔታውን ከማባባስ በስተቀር ምንም መፍትሄ አይሰጥም፡፡ "መሬት ላራሹ" በሚባለበት ጊዜ ከሶርቱ እስከ 75% የሚሆነውን ለመሳፍንትና ለባላባቶች እንዲያስረክብ የሚገደደው ጭሰኛ ገበሬ ይዞታው የግሉ ሆኖ የላቡን ዋጋ ለራሱና ለቤተሰቡ ያድርግ ማለት እንደሆነ ይታወቃል ታዲያ ደርጉ 'ተራ ገበሬ' የሚለው ይህንን ይሆን ወይንስ መሬት ከባላባቶች እየተከራየ ወይም እየገዛ በዘመናዊ መሳሪያዎች የሚያርሰው 'ኑሮው በአርሻ የሆነው' ከበርቴ ገበሬን ይሆን? ህጉ 'በአስቸኳይ' ይወጣል ሲባልስ ምን ያህል አስቸኳይ ይሆን? ዛሬ ባለመሬትና ጭሰኛ ተፋጧል፤ ዛሬ ነገ እያለ መጠበቅ ሰልችቶታል፡፡ ታዲያ እንደገና ሌላ ተስፋ መስጠት ችግሩ ፊት ላይ እስኪወድቅ መጠበቅ አይደለ?

6ኛውና 7ኛው አሳቦች ስለጤና ጥበቃና ስለትምህርት መስፋፋት ይናገራሉ፡፡ 'የጤና ዘመቻ' ሲባል አቅም የሌለው ሁሉ የህክምና አገልግሎት በነፃ ለማግኘት መቻሉን አይገልጽም፡፡ የህክምና አዋቂዎች፡ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች በገጠርና በከተማ መካከል አሁን ያላቸው አድልዎ መወገድ ይገባው እንደሆነ፡እንዴት እንደሚሻሻልና እንደሚጠፋ ምንም አይነት ፍንጭ አይሰጥም፡፡ በትምህርትም በኩል ቢሆን ለገጠሬውና ለወዝአደሩ ልጅ እንዴት እንደሚዳረስ አያወሳም፡፡ ትምህርት ከስራ ጋር መያያዝ እንደሚገባውና ትምህርት ከግል ይልቅ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንደሚውል የሚያስችል ዘዴ አይተለምም፡፡ እንደዚያው እንደጥንቱ 'ይስፋፋል፡ይደረጋል' ብቻ፡፡ ለውጡ የት ላይ ይሆን?

አንቀጽ 11 ምን ለማለት እንደፈለጉ የማይገባ የቃላት ክምችት ነው ቢባል ብዙ መሳሳት አይሆንም፡፡ 'ህብረት' 'እኩልነት' 'አስተሳሰብ' የሚሉትን ቃላት ጣል ጣል ኢድርገው ተወናበደው ያወናብዳሉ፡፡ የኢትዮጵያ ዋና ችግር የመሳፍንት ታሪክና ቅርስ ዘበኝነት የሆነ ይመስል አንቀጽ 14 ስለ'ባህልና የኪነጥበብ ቅርሳቅርሶቻችን'መደራጀት ያወራል፡፡ ዳቦና ውሃ ላረረበት ሕዝብ ይሄ ምን ይበጀዋል? ለምን ደርጉ የመጀመሪያውን ተግባር በመጀመሪያ ለመስራት እንደማይፈልግ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡

በውጭ ጉዳይም በኩል ገለልተኛ ነን፡ቅኝ ግዛትን እንቃወማለን ወዘተ. ተብሎአል፡፡ ግን የሚፈለገው ከኢምፔሪያሊዝም በተለይ ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ሃይለስላሴ የተፈራረማቸው ስምምነቶች መሰረዝና ፀረኢምፔሪያሊስት መሆንን ያለማወላወል መግለጽ ነበር፡፡ ሌላ ስፍራ እንደ ተመለከተው ወታደራዊው መንግስት የበለጠ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ እንዳያደርገን የሚያሰጋ ነው፡፡

'የደርጉ አሳቦች' በሚባል የወጣው ጽሁፍ በአጠቃላይ ሲታይ እንዳለካቸው ካንድ ወር በላይ ሲንደፋደፍበት ከከረመው የሚጭበርበሪያ መመሪያው፡ሃይለስላሴ የአምስት አመት ፕላን እያለ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያወናብዱበት ከነበረው ብዙ አይለይም፡፡ ነገሩ ከእጅ አይሻል ዶማ አይነት ነው ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም፡፡ የሚፈለገው መሰረታዊ ለውጥ ነው ጋይስ ላይ ላዩን ኪፍ ኪፍ፡ነካ ነካ፡ አገም ጠገም! በእንደዚህ አይነት መንገድ ብዙ መሄድ ይቻላል ይሆን? አይመስለንም፡፡